# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ምርጥ ንግግር

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የምርጥ ንግግር መለያዎችን ዘርዝራችሁ ታቀርባላችሁ።
- በተለያዩ ርእሶች ላይ ተዘጋጅታችሁ የንግግርን ሥርዓት ጠብቃችሁ ትናገራላችሁ።
- የተወሰኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ይዛችሁ በቃል በማጥናት ንግግር ታደርጋላችሁ።
- ከዓረፍተነገር ውስጥ የቃላት ክፍሎችን ተግባር ታመለክታላችሁ።
- የእርባታ መሥራች ምዕላዶችን ሙያ ትለያላችሁ።
- ሀሳባችሁን በጽሑፍ ስትገልጹ ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታቸው ታስገባላችሁ።
- ከተለያዩ ንግግሮች ውስጥ ምሳሌያዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለይታችሁ ፍቻቸውን ትሰጣላችሁ።
- ከተለያዩ ንግግሮች ውስጥ የሚገኙትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት ለይታችሁ ፍቻቸውን ታቀርባላችሁ።
- የተወሰኑ ቅኔዎችን ኅብረቃል ለይታችሁ ሰምና ወርቃቸውን ትፈታላችሁ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የምርጥ ተናጋሪ ጥበብ እንዴት ያለ ነው?

፪. ስለ ጥንት የግሪክ ሥልጣኔ አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

፫. ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንዴት ያሉ ጥቅሞች አሉት?

፬. አንድ ንግግር የአድማጩን ቀልብ ሊስብ ወይም ላይስብ የሚችልባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## ዴሞስቴን፣ የምርጥ ንግግር አባት!

ዛሬ፣ የዓለም ሥልጣኔ በደረሰበት ደረጃ፣ የሕዝብ መሪዎች የመንግሥት መማክርት በሚገኙበት ጉባኤ፣ ወይም ሕዝብ በተሰበሰበበት ሸንጎ አን ደበተ-ርቱዕ በመሆን የደጋፊዎቻቸውን መንፈስ በንግግራቸው እየቀሰቀሱ ልባቸውን ለመማረክ ብርቱ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህ ጥረታቸው የሰመረ የሚሆነውም የጥሩ ንግግር ስጦታና ችሎታ ባለቤቶች ሆነው ሲገኙ ነው። የጥሩ ተናጋሪነት ችሎታን እንደሌሎቹ ጥበቦች ሁሉ በትምህርት ቤት ውስጥ ባላሰለሰ ልምምድ ማፍራት ይቻላል። ለመሆኑ በግሪክ ሥልጣኔ ውስጥ ንግግር እንዴት ያለ መድረክ ነበረው?

በግሪክ የቀድሞ ሥልጣኔ ውስጥ፣ ንግግር እንዴት ያለ ተቀባይነት እንደነ በረው ለማውሳት ግሪካዊውን ዴሞስቴንን ማስታወስ የግድ ይላል። ዴሞስቴን፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፫፻፹፬ ተወለደ፤ በ፫፻፳፪ ሞተ። የዴሞስቴን ታሪክ የንግግር ጥበብ ለማስተማር ስለሚያስችል፣ ለምን ተናጋሪ ለመሆን እንደፈለገና እንዴት ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንደቻለ በተከታዩ ታሪኩ እንመለከታለን።

ዴሞስቴን በሕጻንነቱ አባቱ ሞቱበት፤ በዚህም ምክንያት ባለአደራዎች ሆነው የአባቱን ገንዘብ የተረከቡት ሰዎች ገንዘቡን አባከኑበት። ለአቅመ አዳም ሲበቃ፣ ከአባቱ በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ያባከኑበትን ሰዎች ከሶ የአባቱን ሀብት ለማስመለስ ያስብ ነበር። አንድ ቀን፣ የዴሞስቴን

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

አስተማሪዎች በዘመኑ ንግግር አዋቂ በመሆን ይመሰገን የነበረውን ክሊስትራት የሚባለውን ሰው ሲናገር ለመስማት ወደ ሸንጎ ሲሄዱ፣ ዴሞስቴንም ከነርሱ ጋር ንግግሩን እንዲያዳምጥ አስከተሉት፡፡

ዴሞስቴን ክሊስትራት የሚባለውን ሰው ንግግር በመስማትና በሸንጎ ላይ በነበሩ ሰዎች ዘንድ ምን ያህል እንደተደነቀ በማስተዋል፣ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ብርቱ ስሜት በውስጡ አደረ፡፡ እንዲያውም ዴሞስቴን ወደ ንግግር ጥበብ የተሳበው ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደሆነ የሚናገሩ ሰዎች አሉ፡፡

ግሪክ፣ የባለቅኔዎች፣ የፈላስፎች፣ የሊቃውንት እና የደራሲያን አገር በመሆኗ፣ ለማንኛውም ሰው ቢሆን በአቴና ሕዝብ ዘንድ ቀርቦ በጉባኤ ፊት ለመናገርና ተሰሚነት ለማግኘት፣ ከዚህም በላይ ደግሞ ምርጥ ተናጋሪ ሆኖ ለመመስገን፣ ቀላል ነገር አልነበረም፡፡ በዚህ ሁኔታ ዴሞስቴን በመጀመሪያ ጊዜ በጉባኤ ፊት ቀርቦ ሲናገር፣ ንግግር የማይችል ሆኖ ስለተገመተ፣ ንግግሩን እያቋረጡበት “እንዲህ ይባላል፤ እንዲህ አይባልም” በሚል ዓይነት ሁለት ጊዜ አስደገሙት፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ዴሞስቴን ሲናገር ድምጹ ደካማ፣ ምላሱ ኮልታፋ እና ትንፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ የሚል፣ አጭር፣ ስለነበር ንግግሩ እየተቆራረጠበት በሰዎች ዘንድ ሊደመጥ የማይችል እና የማይገባ ሆኖ በመገኘቱ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ፣ ዴሞስቴን ከሰው ተለይቶ እንደ ባሕታዊ ብቻውን እየኖረ ንግግር የማሳመርን ጥበብ ይማር ጀመር፡፡ የሚንተባተበውን ምላሱን ለማፍታታት ሲል፣ ባፉ ውስጥ ጠጠር እየጨመረ፣ ብቻውን ሆኖ እንደ እብድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ በመናገር አንደበቱን ገራው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ፣ በጉባኤ ፊት ቀርቦ በሚናገርበት ሰዓት፣ ሕዝብ ንግግሩን ለማቋረጥ የሚያደርግበትን የተቃዋሚነት ሁካታ ለመልመድና ለማሸነፍ እንዲረዳው ሲል፣ ከባህር ዳር ቆሞ በመናገር የባሕሩ ማዕበል ሲመታው ከሚያሰማው ጩኸት ጋር ንግግሩን ያወዳድር ነበር፡፡ በመሬት ውስጥ

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

የሚኖርበትንም ዋሻ አዘጋጅቶ፣ ብዙ ወራት ሙሉ ከዚያ ሳይወጣ፣ ሰው ሀሳቡን በመልካም ንግግር የሚገልጥበትን ዘዴ ሲሻ፣ ቱሲዳድ የሚባለው ሊቅ የጻፈውን መጽሐፍ እየደጋገመ እስከ ስምንት ጊዜ ይገለብጥ ነበር፡፡ ከተደበቀበትም ጉድጓድ ውስጥ ወጥቶ፣ ሕዝብ ወደሚገኝበት ቦታ የመሄድ ሀሳብ በመንፈሱ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ፣ የራሱን ጠጉር ግማሹን ተላጭቶ፣ ግማሹን ትቶ ከሰው ዘንድ ሊቀርብ የማይችል አስቀያሚ መልክ ይዞ ኖረ፡፡

ዴሞስቴን ይህን በመሰለ አኳኋን ብቻውን እየኖረ፣ ራሱን ለራሱ መምህር አድርጎ በማሰብና በመመራመር፣ ቃላቱን ከፍ አድርጎ ብቻውን በመናገር፣ በመጻፍና በመገልበጥም ስምንት ዓመት ሙሉ መንፈሱን እያበለጸገ አንደበቱን ካረመና ምላሱን ካሰላ በኋላ፣ እንደገና ጉባዔ ፊት ቀርቦ ተናገረ፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ንግግሩን ሲሰሙ እጅግ አድርገው ተደነቁ፤ ዴሞስቴንም አስቦበት ከነበረው ዓላማ ደረሰ፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣ 1994፣ 31-32 ለማስተማሪያ እንደሆን መለስተኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ)*

## ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ በመስጠት በቃል መልሱ፡፡**

1. በጥንታዊው የግሪክ ሥልጣኔ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንዴት ያሉ ዝግጅቶችን ይጠይቃል?
2. ባለንበት ዘመን አስፈላጊ ምክንያቶች አቅርቦ በሰላ (በጠነከረ) አንደበት አድማጮችን መሳብ ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንዴት ይቻላል?
4. ከግሪክ ጥንታዊ ሥልጣኔ ጋር በተያያዘ የዴሞስቴንን ታሪክ ማጥናት ለምን ይጠቅማል?

© MoE, FDRE Not to be rep

2. በዚህ ዘመን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንደ ጥንታዊው ግሪካዊ ዴሞስቴን ከሰዎች ተገልሎ ለብቻ በመሆን ንግግር መለማመድ አስፈላጊ ይሆናል? እንዴት?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን መሰልጠን ወይም መገራት ያለባቸው የአካል ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
4. ዴሞስቴን ራሱን ወደጥሩ ተናጋሪነት ለማሸጋገር ያደረጋቸው ጥረቶች ምንድን ናቸው?

**፪. በቀረበላችሁ ምንባብ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገዉ ዋና መልእክት (ጭብጥ) ምንድነው? በአጭሩ ግለጹ፡፡**

**፫. ለሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች በተብራራ መንገድ ስጡ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. የንግግር ጥበብ | 4. አንደበተ - ርቱዕ |
| 2. የተገራ አንደበት | 5. መንፈስ ማበልጸግ |
| 3. የታረመ አንደበት | 6. ምላስ ማስላት |

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

**፩. ዴሞስቴን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ያደረጋቸው ጥረቶች ተገቢነት እንዳላቸዉና እንደሌላቸው የሚያስረዳ የጋራ ውይይት አካሂዱ፡፡**

**፪. በምርጥ ንግግር አቀራረባቸው የምታደንቋቸው ሰዎች (መምህሮቻችሁ፣ የክፍል ወይም የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ወይም ሌሎች) የንግግር አቀራረባቸው (በይዘትና በቅርጽ) እንዴት እንደሆነ በመዘርዘር ክፍል ውስጥ ተወያዩ፡**

**፫. ቡድን መሥርታችሁ፣ ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ከማንበብና ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ አጥንቶ በቃል ከመናገር የትኛው አድማጭን ማርካት እንደሚችል ተወያዩ፡፡**

© MoE, FDR
Not to be rep

## የንግግር መመሪያ

በመድረክ ላይ የሚቀርብ ንግግር (የመድረክ ንግግር ሊባል ይችላል) በሚከተሉት መመሪያዎች መሠረት ይዘጋጃል፤ ለመድረክም ይቀርባል፡፡

**ሀ. የንግግር አዘገጃጀት**

- የንግግር ርዕስ መምረጥ፣
- የንግግርን ርዕስ መወሰን ወይም ማጥበብ፣
- የንግግሩን ዓላማ በግልጽ መረዳት፣
- የአድማጭን ማንነት መለየት፣
- ንግግር በሚደረግበት ርዕስ ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ማሰባሰብ፣
- መረጃን የሚያመለክት ሀሳብ በአስተዋጽኦ መልክ ማዘጋጀት፣
- በመድረክ ላይ የሚቀርበውን ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ መለማመድ፤

**ለ. የንግግር አቀራረብ**

- አድማጮችን በሚያረካ መንገድ ንግግር ማድረግ፣
- ንግግር በማቅረብ ሂደት ውስጥ የአድማጮችን ሁኔታ በመከታተልና የንግግሩ ሐሳብም ሆነ አቀራረቡ ማራኪ እንዲሆን ማድረግ፡፡
- በንግግር ማቅረብ ሂደት የመግቢያ፣ የዝርዝር ሐሳብና የማጠቃለያ ሐሳብ እንዴት ያለ አቀራረብ ሊኖረው እንደሚገባ አስታውሶ መተግበር

*(ዓለም እሸቱ፣ 1999፣ 130-123 ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ በማድረግ የተወሰደ)*

**፬. የሚከተለውን በጽሑፍ የቀረበ ንግግር መነሻ በማድረግና ተያያዥነት ያለው ሐሳብ በመጨመር ለጓደኞቻችሁ የቃል ንግግር አድርጉ፡፡**

ይድነቃቸው ተሰማ በ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸውን ሙሉ ከስፖርት ዓለም ያልተለዩት ይድነቃቸው ተሰማ ከአገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ የስፖርት አስተዳደሮች በብዙ ቦታዎች ሠርተዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰውነታቸው በህመም በተዳከመበትና በህይወት ለመቆየት አስጊ

ደረጃ ላይ በነበሩበት ጊዜ እንኳ፣ ከሦስት ዓመት በላይ በፕሬዝዳንትነትና በምክትል ፕሬዝዳንትነት ያገለገሉትን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደረሽን (CAF) እንቅስቃሴ ከማገዝ አልተቆጠቡም ነበር፡፡

በኢትዮጵያ ሬድዮ እረጅም ዓመት በተወዳጅ የስፖርት ጋዜጠኝነት ያሳለፈው አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ፣ ይድነቃቸው ከታላቅ ተጫዋችነት፣ አሠልጣኝነትና መሪነት በተጨማሪ የተዋጣላቸው ተንታኝ፣ የአድማጭን ጆሮ መሳብ የሚችሉ ተናጋሪ እንደነበሩ መስክሯል፡፡ በዓለም ዋንጫና በአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ወቅት የይድነቃቸው ተሰማ ትንታኔ ይናፈቃል፡፡ የስፖርት ክሥተቶች ታሪካዊ ቅደም ተከተል የማይዛነፍባቸው፣ የግለሰቦችን ስምና የሚገኙበትን ክለብ፣ መቼና ምን እንደሆነ ሳይቀር፣ ዐውደ ጥበባዊ በሆነ የመረጃ ስፋትና ምርጥ ቃላት፣ ኅሊና ገዥና አሳማኝ ንግግር፣ ትንታኔ የማቅረብ ችሎታ ነበራቸው፡፡

ይድነቃቸው ተሰማ ለማንበብ  የማይታክቱ ሰው መሆናቸው ሌላው ተሰጥኦዋቸው ነበር፡፡ በነጋ በጠባ ቁጥር "ዓለምና ስፖርት እንዴት አደሩ?" ብለው ሳይጠይቁ ወደ ሌላ ተግባር አይሸጋገሩም ነበር፡፡ ከንባብ ቋሚ ልምዳቸው ጋር በተያያዘ፣ እንደ ሁነኛ ውጤት ሊጠቀሱላቸው የሚችሉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ያረቀቁና የጻፉ ናቸው፡፡ ለሕዝብ ታትሞ በመውጣት ደረጃ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለውም፣ "ሕዝብና አስተዳደር፣ ሞራል" የተሰኘው መጽሐፋቸው ነው፡፡

ለይድነቃቸው ስፖርት ምን ጊዜም ለሕዝቦች የእርስ በርስ መቻቻልና የሰላም ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በእምነትና በዘር ላይ የተመሠረቱ ክለቦች እንዳይኖሩ መጣር፣ ቀዳሚ ዓላማቸውና ተግባራቸው ነበር፡፡ ለደቡብ አፍሪካ የፀረ-አፓርታይድ ትግልም ስፖርቱን በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ እኚህ ታሪካዊ ሰው በአፍሪካ የስፖርት "ኮንፍረስ"፣ በዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፣ በ"ፊፋ"ና በአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በፕሬዝዳንትነትና በሌሎች ከፍተኛ የአመራር ሃላፊነት ቦታዎች ሁሉ ተመድበው አገልግለዋል፡፡ ከነዚህ ሁሉ አገልግሎቶች በኋላ በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

*(ሰለሞን ጥላሁንና ስምረት ገብረ ማሪያም፣ 2000፣125-127፣ ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መለስተኛ ለውጥ ተደርጐበት የተዘጋጀ)፡፡*

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

**፫. የሚከተለውን በጽሑፍ የቀረበ ሀሳብ በቃላችሁ በማጥናት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡ (ጽሑፍን አጥንቶ በቃል ስለማቅረብ በምዕራፍ አምስት የተሰጠውን ማስታወሻ እንደገና ተመልከቱ)**

## ዲን ሱዊፍት

ዲን ሱዊፍት የሚባለዉ የእንግሊዝ ደራሲ፣ አዲስ አሽከር በቀጠረ ቁጥር እንዲህ ይለው ነበር፡፡ «እንድትፈጽማቸው የምለምንህ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ የምለምንህ ነገር፣ ምን ጊዜም ቢሆን በቤትህ ውስጥ ስትተላለፍ ከአንዱ ክፍል ወጥተህ ወደአንደኛው ክፍል ስትገባ በሩን እንድትዘጋ ነው፡፡ ሁለተኛው የምለምንህ ነገር፣ እንደዚሁ ሁሉ፣ ካንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ ደጅ ስትሄድ የከፈትኸውን ቤት ዘግተህ እንድትሄድ ነው፡፡»

አንዱ አገልጋይ፣ ከዕለታት አንድ ቀን፣ ወደሱ ዘንድ ቀርቦ፣ «እኅቴ ልትዳር ነውና ለሰርግዋ እንድሄድ ፍቀድልኝ» አለው፡፡ ዲን ሱዊፍትም ደስ እያለው ፈቀደለትና እሱ ከሚቀመጥባቸው ፈረሶቹ አንደኛው ተጭኖለት፣ አንድ ሌላ አገልጋይ ተከትሎት ሄዶ ከቤቱ አድርሶት እንዲመለስ አዘዘ፡፡ አገልጋዩም ከደስታ ብዛት ጌታው ያስጠነቀቀውን ትእዛዝ ዘንግቶ በሩን ከፍቶ ሳይዘጋው ሄደ፡፡ ከሄደ በኋላ ጥቂት ቆይቶ፣ ዲን ሌላ አገልጋይ ጠራና "ፈረስ ጭነህ ጋልበህ ድረስባቸውና ምንም ያህል ርቀው ቢሄዱ፣ ከደረሱበት ቦታ ተመልሰው በፍጥነት እንዲመጡ ንገራቸው" ብሎ ላከው፡፡

የተላከው አገልጋይ በፈረስ ጋልቦ ግማሽ መንገድ እንደሄዱ ደረሰባቸውና የጌታውን ትእዛዝ ነገራቸው፡፡ ፈቃድ ተቀብሎ የነበረው አገልጋይ «ምክንያቱ ምን ይሆን?» እያለ ደንግጦ እየሰጋ ተመልሶ መጣ፡፡ ከጌታውም አጠገብ ቀርቦ፣«እነሆ ተመልሼ መጣሁ፤ ትእዛዝዎን ይስጡኝ» አለው፡፡ ዲን ሱዊፍት፣ «አይ የጠራሁህ ለሌላ ነገር አይደለም፡፡ ከፍተህ ትተኸው የነበረውን በር ዘግተህ እንድትሄድ ነው፡፡» ብሎ መለሰለት፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣1994፣20-21)*

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል ሦስት:- ጽሕፈት

**፩. የሚከተለው አንቀጽ ሥርዓተ ነጥቦች የሚገቡባቸው 14 ክፍት ቦታዎች አሉት:: የቀረበውን ታሪክ በጥንቃቄ በማንበብና የተሰጡት 4 ሥርዓተ ነጥቦች የት የት ቦታ እንደሚገቡ በማጤን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በክፍት ቦታዎች ላይ ሙሉ::**

1. አራት ነጥብ (::)
2. ነጠላ ሰረዝ (፣)
3. ቅንፍ(   )
4. ትእምርተ ጥቅስ (« »)

በጣልያን ወረራ ዘመን ለሀገራቸው ነጻነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር_1_ ዘርጋ ናጂ_2_ ቁመቱ ረጂም_3_ አጥንቶቹ ሰፋፊ _4_ መልኩ ቀይ _5_ ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሦስትዮሽ የተሸረበ ነበር _6_ ያ ፀጉሩ በጀርባውና በትክሻው ላይ ተንዠርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናጽፈዋል _7_ ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆን _8_ ጠቅላላ ገጽታው የሰው ዓይን የሚማርክ ሸበላ _9_ ቆንጆ _9_ ነበር _10_ ዘርጋ ለአራት ዓመታት ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖር _11_ ሹሩባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር _12_ በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሚት ያየችው ሴት ሁሉ _13_ ዐይኔ ይፍሰስልህ _13_ ሳትል አታልፍም ነበር _14_

*(ዓለም እሸቱ፣ ዓለማየሁ ነሪን በመጥቀስ፣ 1999፣ 24)*

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

**፩. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የስም እና የግሥ ሙያዎች ለይታችሁ በመተንተን አሳዩ::**

*ምሳሌ*:- "ሜላት የቤቱን ወለል አጠበች::" በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ስም የሆኑ ቃሎች "ሜላት እና የቤት ወለል" ናቸው:: ስለዚህም የዓረፍተነገሩ:-

ሀ) ባለቤት – ሜላት

ለ) ተሳቢ – የቤቱ ወለል

ሐ) ማሰሪያ አንቀጽ – አጠበች

ይሆናል ማለት ነው።

1. ልጅቷ ላሚቷን አለበች።
2. ህፃኗ ልጅ የመስኮቱን መጋረጃ ጐተተችው።
3. ሠራተኞች የእንስራውን ውሃ ደፉት።
4. ወታደሩ የታጠቀውን ሽጉጥ አወጣ።
5. ችግኞችን ውሃ አጠጣች።

**፪. በሚከተሉት ቃላት ባለንብረትነትን፣የዓረፍተነገር ባለቤትነትንና ተሳቢነትን እንዲያመለክቱ በማድረግ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፣ ዓረፍተነገሮቻችሁንም፣ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማሳየት አስተያየት እንዲሰጡባቸው አድርጉ። በሚሰጥዋችሁ አስተያየት መሠረትም አሻሽላችሁ ጻፉ።**

**ምሳሌ:** • የተሰበረው **ቀንድዋ** ነው። (ባለንብረትነትን)

• **ቀንድ** ለዋንጫ መሥሪያነት ያገለግላል። (ባለቤትነትን)

• ገበያ ወጥቼ **ቀንድ** ገዛሁ። (ተሳቢን)

1. በሬ 2. ልብስ 3. ሴት 4. ውሻ 5. ሥጋ 6. ጽሑፍ

**፫. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች የሚያመለክቱትን (ባለቤትነትን፣ አገናዛቢ አጸፋነትን፣ ተሳቢነትን፣ ብዙ ቁጥርን) ግለጹ።**

ሀ) ተናገረች

ለ) መጽሐፋቸውን

ሐ)ሥራን

መ) ልብሶች

## ክፍል አምስት:- ስነጽሑፍ

**፩. ጥንድ ሁናችሁ ከሚከተለው አንቀጽ ውስጥ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸው አምስት ቃላት አውጡና እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ስጡ።**

ከዱሮ የእንጨት ጉምሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ፣ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ፣ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት፣ የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው። ተበጀ፣ በዚያው በቤቱ

© MoE, FDR
Not to be rep

ውስጥ፣ በዚያው በጉለሌ የተወሰኑ ዘመናት ኖሯል፡፡ እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሠራው እርሱ ነው፡፡ ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል፡፡ ተበጀን፣ ኩራት ተሰማው፡፡ ቆይቶ ደግሞ፣ ዓይኖቹ እንባ አዘሉ፡፡ በጉንጮቹም የእንባ ዘለላዎች ወረዱ፡፡ በግራ እጁ መዳፍ በጉንጮቹ ላይ የተንከባለሉትን የእንባ ዘለላዎች ጨፈለቃቸው፡፡ ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱት የራሱ ጉጆ ስላለው በልቡ ውስጥ ክብርና ኩራት ተሰምቶት ነው፡፡ ሊነገር በማይችል ደስታ ልቡ ተነክቷል፡፡ዝናብ ያበረራቸው፣ ከቤቱ ጥግ ሊጠለሉ ይችላሉ፡፡ ቤት የእግዚአብሔር ነውና ወጀብ እንዳያገኛቸው ከቤቱ ውስጥ ዝናቡ እስኪያባራ ይቆያሉ፡፡ ተበጀን፣ "ቤትህ ይባረክ" ሊሉት ነው፡፡ እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ "ይህ የማን ቤት ነው?" ብሎ ሲጠይቅ "የተበጀ! ሊባል ነው" አለ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ "ተበጀ የትኛው ነው?" ሲባል "ዶሮ ነጋዴው! ሰከራሙ!"፣ ሊባል ነው፡፡ "አወይ! እኔ ተበጀ፣ ተበላሽቻለሁ" አለና ደነገጠ፡፡ ከዚህ በኂላ "ስለቤቱ ክብር እንኳ፣ መጠጥ መተው ይገባኛል" አለ፡፡

*(ተመስገን ገብሬ፣ 2001፣ 119-120 አነስተኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ)*

**፪. በሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ፈሊጣዊ እና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በቀጣዩ ሰንጠረዥ ዓይነት ለዩና ፍች ከሰጣችኋቸው በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

**ምሳሌ፣**

| ፈሊጥ | ፍች | ምሳሌያዊ አነጋገር | ፍች |
|---|---|---|---|
| የህይወት ስርንጉጥ | ችግር፣መከራ | ስምን መልአክ ያወጣዋል | ስም፣ ለተሰያሚዉ መጪዉን ዕድሉን ያመለክታል፡፡ |
| ሀ. | | | |
| ለ. | | | |
| ሐ. | | | |
| መ. | | | |

በቀድሞ አጠራር ኢሉባቦር ክፍለ አገር፣ ሁሩሙ በምትባል መንደር በ፲፱፻፴፪ ተወለደ፡፡ ‹‹ስምን መልአክ ያወጣዋል›› እንደሚባለው ‹‹ሂካ‹‹ የተሰኘ የተጸውዖ ስም ተሰጠው፡፡ ይህ ‹‹ተርጓሚ›› ለተሰኘው የአማርኛ ቃል አቻ ቀረቤታ ያለው የኦሮምኛ ስያሜ ከ ‹‹ሰውዬው›› ኋለኛ የሥራ ሕይወቱ ጋር የተጣመረ በመሆኑ፣ በርካታዎችን ሳያስደምም አላለፈም፡፡ ምፅዋ ዘልቆ በስመ ጥምቀቱ (በጥምቀት ስሙ) ‹‹ኦኔሲሞስ›› የሚል መጠሪያ የተሰጠው ሂካ፣ በኦሮምኛ ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎችንም ጽሑፎች በመተርጐም ለቋንቋው ሥነጽሑፋዊና ሥነልሳናዊ እድገት ሁነኛ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኦኔሲሞስ ወደዚህ ዓቢይ የትርጉምና ጽሑፍ ሥራ ከመዝለቁ አስቀድሞ፣ መሪርና አስከፊ በሆነ የሕይወት ስርጓጉጥ ውስጥ አልፏል፡፡

“ፀሐይ ሳለ ሩጥ፣ አባት ሳለ አጊጥ” የሚባለው እድል አላጋጠመውም፡፡ ገና የአራት ዓመት ልጅ ሳለ ወላጅ አባቱን ሞት ነጠቀበት፡፡ ድንጋጤው በቀሪው ቤተሰብና በጨቅላው ሂካ ሕይወት የጨለማ ድባብን አጠላ፡፡ የመከራው ገፈት በዚህ ሳያበቃ፣ ተጨማሪ ስቃይና ኀዘን ወደዚህ ጎጆ መንደርደር ጀመረ፡፡

“የመከራ ቀን ሲደርስ አይታወቅም” እንደሚባለው በዘመኑ የድሃውን ጎተራ እየገለበጠ፣ ከብት በዝርፊያ እየነዳ፣ እንደ ቋያ እሳት ቀዬ እያጋየና የሰፈሩን ማቲ ለባርነት እየዳረገ የሚዘዋወር የሽፍታ መንጋ፣ በሁሩሙ መንደር ዘልቆ ጎጡን ማመስ ጀመረ፡፡ ይኼኔ የሂካ ወላጅ እናት፣ “እናት ለልጇ አራስ ነብር ናት” እንደሚባለው፣ ከዚህ መዓት ልጇን ለመታደግ ሽሽት ገባች፡፡ ሆኖም የዕለቱ ጀምበር ፊት ነስቷት ኖሮ፣ ሰይፍ ከሚነቀንቁ የሞት መልእክተኞች ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠች፡፡ በወቅቱ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ የነበረው ሂካ፣ ያቺን ቅጽበት ከጊዜ በኋላ እንዲህ ያስታወሳታል፡፡

“አንድ ሰው እየተንደረደረ መጣና እጄን በመጐተት ወደራሱ ሳበኝ፤፡፡ እናቴም የቀረውን እጄን አጥብቃ በመያዝ፣ ‘ፈጽሞ አትወስደውም!’ ስትል ተከላከለች፡፡ ይኼኔ ሰውዬው ሰይፉን መዘዘና፣ ‘የማትለቂው ከሆነ



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FD
Not to be rep

ሁለታችሁንም እገድላለሁ!’ ሲል ዛተ። እናቴም፣ ‘ከሚሞትብኝ ባርነት ቢገባ ይሻላል።’ በማለት እጁን አላላች”።

በዚህ ዘግናኝ ሁኔታ ከእናቱ መዳፍ ተመንጭቆ በወንበዴዎች እጅ የወደቀበት ቅጽበት፣ ከቶም ከምናቡ እንዳልተፋቀና ውስጡንም ያዋትተው እንደነበረ በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ባሰፈራት ስንኝ አማካይነት መገንዘብ ይቻላል። “ሞትን መሻገር ከተቻለ አዲስ ሕይወትና እድል ይገኛል።” እንደሚባለው፣ወጣቱ “ሂካ” (በኋላ ኦኔሲሞስ ተብሎ የተሰየመው) በህይወት ዘመኑ ብዙ ሥራ ሠርቷል።

*(ሰሎሞን ጥላሁንና ሥምረት ገብረማርያም፣ 2000፣ 22-23)*

## ቅኔ

ቅኔ በቃል ወይም በጽሑፍ በግጥም ወይም በዝርው የሚነገር ወይም የሚጻፍ ድርሰት ነው። ቅኔ መቀኘት ማለትም አመራማሪ የሆነ የተደበቀ ነገር ያለው ግጥም መግጠም፣ ሀሳብን አመራማሪ (ምስጢር) አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው። ቅኔ በግጥም፣ ሲቀርብ አደራደሩ ወይም የምጣኔ ማሳያ ምቱ ምንም ሳይዛነፍ ዜማውን ጠብቆ ቅርጽና ይዘቱን አስማምቶ ከቀረበ ውበቱ በቀላሉ ይታያል፤ አንባቢን ወይንም ቅኔ ፈቺን ይስባል፤እንዲመራመር ያደርገዋል።

ቅኔ የሚነገረው ወይም የሚጻፈው በሰምና ወርቅ ነው።
“ሰሙ ደራሲው ሊናገረው ያሰበው ነገር የተሸፈነበት መጋረጃ ሲሆን፣ ወርቁ ደግሞ አንድን ቃል በማጥበቅ፣ በማላላት፣ ወይም አጠገቡ ካለው ከሌላው ቃል ጋር አያይዞ በማንበብና በመመርመር የሚገኘው ምሥጢር ወይም ፍሬ ነገር ነው”
*(ብርሃኑ ገበየሁ፣ 2001፣ 173)።*

ቅኔው የተመሠረተበት ቃል ኀብረ ቃል ይባላል። ኀብረ ቃሉ በፍች በሁለት ቦታ ተከፍሎ አገባባዊ ትርጉሙ ሰም፣ ከአገባብ ውጪ የሆነው ፍች ደግሞ ወርቅ ይባላል። በዚህም መሠረት የሚከተሉትን ቅኔዎች በምሳሌነት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል።

**ምሳሌ፣**

ምነው ጌታዬ በደልከኝ
አጥፍቼም እንደሁ ሳትመክረኝ፣
በሰው ፊት ቀጣሽኝ ፡፡

ኅብረ - ቃል፣በሰው ፊት
ሰም፣ሰው እያየ
ወርቅ፣ የሰው ፊት እንዳይ፣ እንድለምን ወይም ተረጅ እንድሆን አደረግሽኝ፡፡

**፫. በቡድን በመሆን ከሚከተሉት ቅኔዎች ኅብረ ቃሎችን ከለያችሁ በኋላ ሰምና ወርቅ ብላችሁ ፍቻቸውን በመዘርዝር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ) እንዴት ያለ ሰው ነው የሌለው እምነት፤
እውነት ሞቷል ብለው ይለኛል ሐሰት፡፡

ለ) እኛስ ሄደን ነበር ደጎና አገር መስሎን፤
ተመልሰን መጣን ጉጉት በዝቶብን፡፡

ሐ) እዚያ ማዶ ሆና ትጣራለች እናት፤
ና ብላ ነው እንጂ ሌላም ጉዳይ የላት፡፡

መ) እዩልኝ ያንን ልጅ ጌጥ አልጠግብ ባይ፤
መርገፍ ጨመረበት በጥበቡ ላይ፡፡

ሠ) እያለለት መልኬ ካንገቴ በላይ፤
እጅ እጄን ያየኛል ያለም አታላይ፡፡

ረ) ከልፍኝ አስወጥተው እዳስ አጉረው፤
ቅራሪውን ሰጡኝ ጠላ ነው ብለው፡፡

ሰ) ለልጅ ልጅ ለምልሞ እንዲህ የሚታየው፤
ይህ አትክልታችን አዲስ አበባ ነው፡፡

ሸ) ተዋት አትገላግሏት ሩቅ ነው መንገዷ፤
የከበደ ነገር ይዛለች በሆዷ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ማጠቃለያ

ምርጥ ንግግር የይዘትና የቅርጽ ድምር ነው፡፡ ይዘት የሚነገረው ጉዳይ ሲሆን፣ ቅርጽ ደግሞ አቀራረብ ነው፡፡ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ በበቂ ሁኔታ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ንግግር፣ በጥንቃቄ መዘጋጀት እና በአዘገጃጀቱ ደግሞ ንግግሩ በሚቀርብበት ዓላማ እና በታዳሚዎች ማንነት ላይ ተመስርቶ መደራጀት ይኖርበታል፡፡
ምርጥ ንግግር ከፍተኛ ጥበብ ነው፤ ሀሳብን የማቅረብ ጥበብ፡፡ የንግግር ጥበብ ሀሳብ፣ ቋንቋ እና አቀራረብ ይሻል፡፡

የንግግር ቋንቋ ሲባል፣ ንግግሩ የሚቀርብበትን መደበኛ ሰዋስው፣ ከዚያም አልፎ ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ ምሳሌያዊ አቀራረቦች፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. ግብአት ያደርጋል፡፡ በምርጥ ንግግር ውስጥ፣ የንግግር ታዳሚዎችን ስሜት በአቀራረብ (በአንደበት፣ በአገላለጽ፣ ወዘተ) አጥብቆ መያዝና ወደ ሚፈለግበት አቅጣጫ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ቃላት በዓረፍተነገር ወስጥ የተለያዩ ሙያዎች አሏቸው፤ በባለቤትነት ያገለግላሉ፤ በተሳቢነት ያገለግላሉ፤ በማሠሪያ አንቀጽነት ያገለግላሉ፡፡

ምዕላዶች በዓረፍተነገር ውስጥ በአጸፋ ባለቤትንና ተሳቢን ያመለክታሉ፤ እንዲሁም ባለ ንብረትነትን ይጠቁማሉ፡፡

በጽሑፍ ሀሳብን ለማስተላለፍ ሥርዓተ ነጥቦች በሥርዓት ከተያያዙ ቃላት ጋር በመጣመር አገልግሎት አላቸው፡፡ ስለዚህ በተገቢው ቦታ አስፈላጊውን የሥርዓተ ነጥብ ዓይነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ቅኔ በንግግርም በጽሑፍም ይቀርባል፡፡ ቅኔ ሀሳብን አመራማሪ አድርጎ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የምርጥ ንግግር መለያ ይሆናሉ የምትሏቸውን ሦስት ነጥቦች ጻፉ፡፡
2. በቃል አጥንቶ ንግግር ለማካሄድ በዝግጅት ወቅት ማድረግ የሚገባችሁን ሦስት ነጥቦች ጻፉ፡፡
3. ዓረፍተነገሮችን ስትመሰርቱ የቃል ክፍሎች ተግባር እንዴት ያለ ነው?
4. የእርባታ ምዕላዶች ሙያ እንዴት ያለ ነው?
5. ስርአተ ነጥቦች በጽሕፈት ውስጥ ካላቸው አገልግሎት ሁለቱን ብቻ ጻፉ፡፡
6. ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች በንግግር ውስጥ እንዴት ያለ ጠቀሜታ እንዳላቸው ግለጹ፡፡
7. የቃላት እማሬያዊ ፍች ምንድነው? ፍካሬያዊ ፍችስ?
8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችሁትን በመከተል ለቅኔ አፈታት መግለጫ ስጡ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርጥ ንግግር መለያዎችን አመለክታለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ መዘጋጀትና የንግግር ሥርዓትን መጠበቅ እንደሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የተለያዩ መረጃዎችን በማስታወሻ በመያዝ እና በማጥናት የቃል ጥናት ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በዓረፍተነገሮች ውስጥ የቃላት ክፍሎችን ተግባር መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የርባታ ምዕላዶችን ሙያ የትኞቹ እንደሆኑ መዘርዘር ችያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ሀሳቤን በጽሑፍ ስገልጽ አስፈላጊ ሥርዓተ ነጥቦችን እጠቀማለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ከተለያዩ የንግግር ዝግጅቶች ውስጥ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለይቼ በማውጣት ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ከተለያዩ የንግግር ዝግጅቶች ውስጥ እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት በመለየት ፍቻቸውን ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |
| 9 | ለቀረቡልኝ የተለያዩ ቅኔዎች ህብረ ቃል በመለየት የሰምና የወርቅ ፍቻቸውን ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced